# ዶባዎች፣ ዶባዎች እንጂ ሌላ ሊሆኑ አይችሉም! ራያዎችም እንዲሁ!!

**ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ**

08-30-14

sisayraya@yahoo.com

## እንደ መግለቢያ

ተሾመ ብርሀኑ ከማል የተባሉ ፀሀፊ በሪፖርተር ጋዜጣ ቁጥር 1490 እና 1492 እሁድ ነሐሴ 4 እና 11/2006 ዓ.ም ዕትም ከታሪክ ጥግ በሚለው አምድ ላይ በድንገት ብቅ በማለት ዶባዎች እነማናቸው? ራያዎችስ? በሚል ርዕስ በርካታ የታሪክ ተመራማሪዎችንና የተጓዥ ጸሀፊዎችን ስራዎች አጣቅሰው በሁለት ተከታታይ ክፍል ሰፊ ሊባል የሚችል ሀተታ አቅርበዋል፡፡ ይህም ሊያስመሰግናቸው የሚገባ ታላቅ ስራ መስራታቸውን የሚያመለክት ስለሆነ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን መግለጽ እፈፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም ቢያንስ የዶባዎችን (የራያዎችን) ጉዳይ በግል የህትመት ውጤቶች ላይ ጭምር የመወያያ ርዕስ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታልና፡፡

ጸሀፊው በመግቢያቸው ላይ “ራያዎች ዶባዎች አንጂ ትግራዮች አይደለንምና ልዩ ዞን እንሁን” የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ ከመድረሳቸውም በላይ እንዲህ እንዲሉ ያበቃቸውንም ምክንያት ሲገልጹ አሁን ላይ የራያን ህዝብ የሚያስተዳድሩት የራያ ተወላጆች ስላልሆኑ እነዚህ ሰዎች ከስልጣን ተወግደው በአካባቢው ተወላጆች ልንመራ ይገባል የሚል አመለካከት በመያዛቸው እንደሆነ አድርገው መገንዘባቸውን ያመለክታል፡፡ አያይዘውም ህገ መንግስቱ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለተወሰነ ጊዜ በአንድ አካባቢ ከኖረ፣ ቋንቋውን ካወቀና ባህሉን ከተቀበለ መምረጥም ሆነ መመረጥ መብቱ ነው፡፡ ስለዚህ የሚመረጠው ሰው ምርጫ ቦርድ ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከተወዳደረና የህዝብን አመኔታ አግኝቶ ከተመረጠ “መመረጥ የለበትም” ሊባል አይችልም፣ የሚል የመከራከሪያ ሀሳብም አንስተዋል፡፡

እውነት ነው ህጉ በሚፈቅደውና በምርጫ ቦርድ የተቀመጠውን አሰራር በተከተለ መልኩ ቢኬድ ኖሮ ራያዎችም ያን ያህል ባልተከፉ ነበር፣ ችግሩ ያለው የከተማ ከንቲባዎችም ሆኑ የወረዳ አስተዳዳሪዎች በአካባቢው ኖረውና ጸሀፊው እንዳሉት በራያ ህዝብ አመኔታ አግኝተው በመመረጥ ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ ወደ ስልጣን የሚመጡት በበላይ አካል ውሳኔ ከሌላ አካባቢ መጥተው በላያቸው ላይ የሚቀመጡ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአንድ አካባቢ አከላለልን በሚመለከትም የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ታሪክን ወይም መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥን ሳይሆን ቋንቋን መሰረት ያደረገ ነው በማለት ሊከራከሩ ይሞክራሉ፡፡ እዚህ ላይ ጸሀፊው ህገ መንግስቱን በሚገባ ሳያውቁና ሳያገናዝቡ እሳቸው ለሚፈልጉት ሀሳብ ማሟያ ለማድረግ ብቻ በልበ ብርሀንነት እንደሚጠቅሱት ከማሳየት አልፎ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም፡፡

ለትክክለኛ ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 46 (3) የሚለውን ቀጥለን እንመልከት “ክልሎች የሚዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነው” ይላል፡፡ ታዲያ አቶ ተሸመም ሆኑ መሰሎቻቸው ከላይ ያጣቀሱትን ምናብ ወለድ ሀሳብ ከየት አመጡት? ቀጠል አድርገውም በአንድ አካባቢ ክልል ወይም ዞን ለመመስረት ወይም የፖለቲካ መዋቅር ለመዘርጋት ከተፈለገ አሁን ባለው ህገ መንግስትም አብዛኛው ህዝብ የሚናገረው ቋንቋ

ምንድ ነው የሚለውን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርበታል ሲሉ በህገ መንግስቱ በግልጽ ተለይቶ ያልሰፈረን ሀሳብ ነገር ግን እሳቸውና መሰሎቻቸው እንዲሆን የሚፈልጉትን አመለካከት ለማስረጽ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ ራያዎች ራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር መብት ማግኘት ይገባናል! የሚለውን ጥያቄ ውስጥ ለውስጥና በመጽሀፍ መልክ አሳትሞ ማውጣት ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ካነሱ በኋላ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ የሚነሳው ቅሬታ ከመልካም አስተዳደር እጦት (ከአስተዳደር በደል) ጋር ሊያያዙ ይላሉ በማለት የመሰረታዊ ችግሩን ስፋትና ጥልቀት አሳንሰው ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡

እኚህ ጸሀፊና መሰሎቻቸው አንድም የመረጃ እረት አለባቸው አሊያም ሆን ብለው ለማድበስበስ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም ማንም ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው እንደሚችለው ራያዎች ድሮም ሆነ ዘንድሮ ውስጥ ለውስጥ መሄድን አያውቁበትም፣ ራያዎች ከክልሎች ምስረታ ወቅት አንስቶ በተለይም ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ በተለያዩ መድረኮች ላይ ጥያቄውን በማንሳት የተከራከሩ የአካባቢው ተወላጆች ከመኖራቸውም በላይ ሰሚ አልተገኘም እንጂ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአደባይ ጥያቄውን አንስተው ሲከራከሩ ታዲያ አማሮች ከሆናችሁ ለምን ወደ አማራ ክልል አትሄዱም እስከመባል ደርሰው የነበረበት ጉዳይ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

ከዚህም አልፎ ተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፎቻቸውን በአካባቢያቸው ላይ እንዲያተኩር በማድረግ እውነተኛውን የራያን ህዝብ ታሪክ ፈልፍለው ማውጣት በመጀመራቸውና አለፍ ሲልም በመጽሀፍ መልክ አሳትመው በማውጣታቸው አይደለም እንዴ ጸሀፊውን ጨምሮ የተንሸዋረረ ብዕራቸውን ሳይቀር አንስተው ለማስተባበል ጥረት እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው፡፡ በመቀጠልም የአስተዳደር በደሉ ፖለቲካዊ መሆኑ ቀርቶ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ቀለም፣ ዘር፣ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ ከሆነ ደግሞ "እኛ ዶባዎች ነን" ከሚለው እንጀምር በማለት ወደ ተነሱበት አላማ ለመግባት ስለፈለጉ ብቻ ለመሆኑ ዶብአዎች ወይም ዛሬ እንደሚባለው ዶባዎች እነማናቸው? ራያዎችስ? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ታሪክን በማጣቀስ ሰፋ ያለ ማብራሪያቸውን አቅርበውልናል፡፡

በተለይም በራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄና የማዕከላዊ መንግስታት ምላሽ ከአጼ ዮሀንስ 4ኛ እስከ ኢህአዴግ በሚል ርዕስ በአለሙ ካሳ ረታና በሲሳይ መንግስቴ አዲሱ ተጽፎ ነሀሴ 2005 ዓ.ም ላይ ታትሞ ለአንባቢያን እንዲደርስ በተደረገው መጽሀፍ ውስጥ የተጠቀሰን አንድ አረፍተ ነገር ብቻ አንስተው ማለትም አፋሮች አጼ በዕደማሪያምን ወግነው ዶባዎችን ስለወጉ ከአፋር የተለዩ ጎሳዎች አንዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሀሳብ መቅረቡንና የአፋር ብሔረሰብ አካል ቢሆኑ ኖሮ የአብራካቸው ክፋይ የሆኑትን የአፋር ብሔረሰብ አባላት ያን ያህል ጨክነውና ራሳቸውን እንደ ባዕድ ብሔር በመቁጠር በተደጋጋሚ ወደ አካባቢያቸው እየዘመቱ በጦር ሀይል አይወጓቸውም ነበርና ነው ማለታቸው በአንድ ብሔር ህዝብ መካከል ከሚደረግ የገዥዎች እርስ በርስ ግጭት ጋር አገናዝበው ለመረዳትና ይህም ሁኔታ ቀደም ሲል ጀምሮ የነበረና አሁንም ቢሆን ሊያጋጥም የሚችል ስለሆነ ይህ ሁኔታ ብቻ ዶባዎችን ከአፋር የተለዩ ህዝቦች እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው አይችልም በማለት የመከራከሪያ ሀሳባቸውን ለማጠናከር ሞክረዋል፡፡

እርግጥ ነው የኢትዮጵያ ታሪክ በእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት የታጀበ ነው ሲባል በአንድ ብሔረሰብ መካከል የሚካሄደውን የእርስ በርስ ጦርነት የሚያካትት መሆኑ ላይ ሁላችንም የምንስማማበት ጉዳይ ነው፣ ሆኖም ይህ ሁኔታ በአብዛኛው የሚከሰተው በገዥዎች በራሳቸው አሊያም በእነሱው አነሳሽነት እንጂ እንደ ህዝብ እርስ በርስ እንደማይጨፋጨፉ ጸሀፊውም

ለአላማቸው ማሳካያ ያገለግል ይሆናል ብለው በማሰብ ያነሱት ሀሳብ ይሆን እንደሆነ እንጂ ዘንግተውት አይመስለኝም፡፡ አቶ ተሸመ ጽሁፋቸውን ሲያጠቃልሉም ዶባዎች አሁንም ድረስ በህይወት መኖራቸውን ከአረጋገጡ በኋላ የተነሱበትን አላማ አስረግጠው ለመግለጽ ስለፈለጉ ብቻ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የሐሸንጌና አካባቢው ሰዎች ትግርኛ እንጂ አፋርኛ ተናጋሪዎች አይደሉም፡፡ ራያዎችም በአብዛኛው ትግርኛ እንጂ ዶብኛ ወይም አፋርኛ ወይም ሳሆኛ ወይም በአብዛኛው ኦሮምኛ ተናጋሪ አይደሉም፡፡ በ1960ዎቹ ከፊል አማርኛና ትግርኛ ይነገርባት የነበረችው ዋጃ ከተማ እንኳ ዛሬ በአብዛኛው ትግርኛ ተናጋሪዎች ይኖሩበታል፡፡ በማለት መረጃ አልባ ሀሳባቸውን በድፍረት ከመግለጻቸውም በላይ እና ምን ማድረግ ይቻላል የሚል ጥያቄ ካነሱ በኋላ ለጥያቄው ሀላፊነት የተሞላበት መልስ ከመስጠት ተቆጥበው የተሰጣቸውን "ምሁራዊ" ተልዕኮ ለመወጣት በማሰብ ምንም ሲሉ ጥያቄውን አቃለው ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡ ቀጠል በማድረግም መልሱ ምን መሆኑ ይቅርና ዶባዎች የራሳቸው አስተዳደር ይመስርቱ እንበል፣ መሰረቱም፣ ከዚያስ ከዚያማ ሌሎችም ዘር እየቆጠሩ የራሳቸውን ክልል መመስረት ነው፡፡ በማለት የጥያቄውን መሰረታዊ ይዘት በማዛባት ጭምር የአንድነት ጠበቃ ለመምሰል ይሞክራሉ፡፡

ይሁን እንጂ ከፌዴራል ስርአቱ መመስረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን ፖለቲካዊ አደረጃጀት ስንመለከት ሌላውን ትተን የሀረሪ ክልል የተቋቋመው በዘርና በታሪክ ላይ ተመስርቶ እንጂ አሁን ያለው አብዛኛው ነዋሪ ህዝብ የሚናገረው ቋንቋ ግምት ውስጥ ቢገባ ኖሮ የሀረሪ ክልል በኦሮምያ ክልል ውስጥ አንድ ወረዳ አሊያም በኦሮሞዎችና በአማሮች ጥምረት የሚተዳደር ልዩ ወረዳ/ዞን በሆነ ነበር፡፡ እሩቅ ሳይሄዱም ትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙትን የኢሮፕና የኩናማ ብሔረሰብ አስዳደር አደረጃጀትን ቢመለከቱ በቋንቋና በዘር ላይ መመስረቱን በአግባቡ በተገነዘቡ ነበር፣ ታዲያ ምን ያደርጋል ለእሳቸው የአንድነት አደጋ ሆኖ የታያቸው የራያዎች ራስን በራስ የማስተዳደርና የማንነቴ ይታወቅ ጥያቄ እንጂ የሌላውማ ያን ያህል ቁብ የሚሰጣቸው አልሆነም፡፡

በአናቱም ስለዚህ ምን ይደረግ የሚል ጥያቄ በድጋሜ ካነሱ በኋላ የሚሻለውማ ችግሩ የአስተዳደር ችግር ከሆነ በሚቀጥለው ምርጫ ማስተካከል ዴሞክራሲያዊ መብት ነው በማለት የውስጣቸውን በውስጣቸው አድርገው በራያ ህዝብ ላይ ለማፌዝ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ህገ መንግስት መንፈስ በአግባቡ ሳይረዱ በቋንቋ እንጂ በዘር ላይ የተመሰረተ አይደለም በማለት ሲከራከሩ በሌላ በኩል በፍጹም በመሬት ላይ የሌለን ሀቅ የዋጃ ከተማን ሳይቀር በምሳሌነት በማንሳት አካባቢው በአብዛኛው የትግርኛ ተናጋሪዎች መኖሪያ ነውና ትግራዮች አይደለነም የምትሉትን ነገር እርግፍ አድርጋችሁ በመተው ጭምር አርፋችሁ ተቀመጡ በማለት "ጉንጭ አልፋ" የሆነ የመከራከሪያ ሃሳብ ይዘው ብቅ አሉ፡፡

የሚገርመው ነገር በአንድ በኩል ራያዎች ያነሱት የዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብታችን ይከበር ጥያቄ በአግባቡ ቢመለስ ኖሮ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትም ሆነ የህዝቦችን የእርስ በርስ መልካም ግንኙነት ይበልጥ ሊያጠናክር የሚችል ካልሆነ በስተቀር ሌላ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል እንደማይችል እየታወቀ በሌላ በኩል ደግሞ የራያ አላማጣ ወረዳ የዋጃ-ጥሙጋ ከተማን ጨምሮ አራት ቀበሌዎችና የራያ አዘቦ ወረዳም አራት የገጠር ቀበሌዎችን በመለየት አማርኛ ተናጋሪ ህዝቦች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን በማረጋገጥ ጭምር የአካባቢዎቹን ነዋሪዎች ሰብስበው ለማወያየት ሲፈልጉ አማርኛ ቋንቋ የሚችል ካድሬዎች ወደ ስፍራው እየተላኩ በአማርኛ ቋንቋ እንዲያወያዩ እየተደረገ ባለበት በአሁኑ ወቅት እውነታውን ያላገናዘበና "አልሰሜን ግባ በለው" ሊያሰኝ የሚችል ሀሳብ ይዞ ወደ አደባባይ መቅረብ በእርግጥ ራስን ትዝብት ውስጥ ከመክተቱና ለሞያም ታማኝ አለመሆንን ከማሳየቱም በላይ የቆሙለት አላማም ትክክለኛ አለመሆኑን ሊያሳብቅ  እንደሚችል አስቀድሞ መገመት ብልህነት ይመስለኛል፡፡

ይህን ጥቅል ሀሳብ እዚህ ላይ ገታ እናድርገውና ለመሆኑ ዶባዎች እነማናቸው? ራያዎችስ? የሚለውን መሰረተ ሀሳብ በሚመልስ መልኩ ቀጥሎ ባለው ንዑስ ምዕራፍ ታሪካዊ ዳራውን በአጭሩ እንፈትሸው፡፡

## ለመሆኑ ዶባዎች እነማን ናቸው? ራያዎችስ?

ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የተባሉ የታሪክ ምሁር ህዳር 26 ቀን 1991 ዓ.ም "የኢትዮጵያዊነት ማህበር" ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ታሪካዊ ንግግር ውስጥ በዕደማሪያም የራያን አካባቢ ቀደምት ህዝቦች እንዴትና በምን አግባብ እንደተቆጣጠሯቸውና እንዳስገበሯቸው ጭምር ሲያስረዱ የሚከተለውን ሀሳብ አቅርበው እንደነበር በማስታወስ ታቦር ዋሚ የተባሉ ጸሀፊ የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች በሚለውና በዚህ አመት ታትሞ ገበያ ላይ በዋለው ዳጎስ ያለ መጽሀፋቸው ገጽ 189-190 ላይ ያስቀመጡትን ሀሳብ እንደሚከተለው በማሳያነት ላቅርብና ዶባዎች እነማናቸው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በርካታ ታሪካዊ ሁኔታዎችን ለማቅረብ ልሞክር፡

"… አጼ በዕደ ማሪያም (1461-1471) … በንግስና ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከአንድ ዶባ እየተባለ ከሚጠራ ህዝብ ጋር ከፍተኛ ጠብ እንደነበረውና በተደጋጋሚ ዘምቶባቸው፣ በመጨረሻ በስልጣኑ ስር እንዳስገባቸው ዜና መዋዕሉ ያወሳናል፡፡ ይህ የዶባ ህዝብ እያመጸ የሚያስቸግረው ባሁኑ ጊዜ ደቡብ ምስራቅ ትግራይና ሰሜን ምስራቅ ወሎ ብለን በምንጠራቸው ወደ አፋር ቆላማ አገር ወደ መውረጃው ላይ ነበር፡፡ በዕደ ማሪያም ከችግሩ የተነሳ የዚህን ህዝብ ቀንደኛ መሪ ጎሳዎች እየመረጠና ከሚኖሩበት አካባቢ እያወጣ በየሌላ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች … በመንዝ መካከል የሚገኘው ታላቁ የሞፈር ወንዝ ሸለቆ ውስጥ አሰፈራቸው፣ የቦታውም ስም ዶባ ተባለ፡፡ ዶባ ከአገር ለምነት አልፎ ታላላቅ የሰሜን ሸዋ መሳፍንት የዘር ሀረጋቸውን በኩራት የሚመዙበት፣ በጣም የተከበረ የዘር ግንድ ሆኗል፡፡ ኦሮሞዎችም ሆኑ ትግሬ የአጼ ኃይለስላሴ ወንድ አያት ደጃዝማች ወልደሚካኤል ጉዲሳ ሳይቀሩ የዶባ ተወላጅ ወይም ማደጎ ናቸው፡፡" ይላሉ፡፡

አቶ ታቦር ሀሳባቸውን አጠናከረው ሲቀጥሉም "ዶባ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የሚገኝ የኦሮሞ ንዑስ ጎሳ ከመሆኑም በላይ የኦሮሞ ህዝብ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ለመኖሩ አንዱ ተጨባጭ ማስረጃ ነው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ዶባ የሚለው ስም እዚህ ቦታ ብቻ ሳይሆን በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በብዙ አካባቢዎች ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ ሐረርጌ፣ በሰሜን ሸዋና በሌሎችም ምዕራብ ኦሮሚያ አካባቢዎች ዶባ የሚል መጠሪያ ያላቸው በርካታ ቦታዎች እንዲሁም፣ የኦሮሞ ንዑስ ጎሳዎች ይገኛሉ፣ በማለት የክርክር ሀሳባቸውን ይበልጥ ያጠናክራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦሮሞዎች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ሲል ጀምሮ በአካባቢው ይኖሩ እንደነበር ማስረጃዎችን በማጣቀስ የሚከራከሩ ወገኖች መኖራቸውን ጠቅሰው ታቦር ዋሚ የሚከራከሩ ሲሆን በዚህ ረገድ ኮንትሮሲኒ ስለ አምደጽዮን ዘመን (1314-1344) በማስታወሻው ላይ የጠቀሰውን በማጠናከር ከላይ በተጠቀሰው መጽሀፋቸው ገጽ 157 ላይ "በሰሜን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ከሰፈሩ የኦሮሞ ራያ ጎሳዎች (ዋጅራት፣ ኢጉይና መረዋ፣ ዶባ፣ አፍላ፣ አሰቦና ቆቦ) መካከል ኢጉይና መረዋ የሚባሉ ኦሮሞዎችን መልምሎ በሰራዊቱ ውስጥ ሲጠቀምባቸው ነበር ብለዋል"::

ይህም ማለት ኢጉይና መረዋ ዋነኛዎቹ ዶባዎች መሆናቸው ግልጽ ነው፣ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ዶባዎችን የትግራይ ብሔር አካል አድርገው ለማሳየት ጥረት የሚያደርጉ የታሪክ ምሁራንና

ተመራማሪዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም መካከል ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይና ጸጋዘዓብ ካሳ በግንባር ቀደምነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆኑ እነዚህ የታሪክ ምሁራን ዶባዎች ትግራዮች (የሴሚቲክ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች) ሊሆኑ እንደሚችሉ በጠንካራ ማስረጃ ያልተደገፈ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ዶባዎች የትግራይ ብሔር ህዝብ አካል እንዳልነበሩና አሁንም ድረስ እንዳልሆኑ ጭምር የሚያሳዩ በርካታ የሰነድ ማስረጃዎች መኖራቸውን በርካታ ጸሀፍት በማሳያነት ያቀርባሉ፡፡ ይህን ሁኔታ አስመልክቶ ክብሮም አሰፋ ሞላ የራያ ህዝብ ታሪክና ባህል በሚለውና በ2005 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ባሳተመው መጽሀፉ ገጽ 32 ላይ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሮ እናገኛለን፡ “ዶባዎች የትግራይ ብሔር አካል ሊሆኑ እንደማይችሉ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፣ በዚህ ረገድ (ግንባር ቀደም) ተጠቃሽ የሆነው በ18ኛው ክፍለ ዘመን የዶባ ህዝቦችን ምድር (ለመጀመሪያ ጊዜ) የረገጠው ተጓዡ ሚስተር ፒርስ በአጼ እያሱ 2ኛ (1730-1755) ከትግራይ አስተዳዳሪ (ራስ) ጋር ተገናኝቶ ወደ ንጉሱ ቤተመንግስት ለመጓዝ በዶባ ምድር ባቋረጠበት ወቅት ከትግራይ አብረውት የመጡት ሁለት አጃቢዎቹና አገልጋዮቹ ከዶባዎች ጋር በቋንቋ ለመግባባት መቸገራቸውን በጉዞ ማስታወሻው ላይ ማስፈሩን ሄንሪ ሳልት ዘግቧል ሲል ያረጋግጣል፡፡”

ከዚህም በተጨማሪ የሄነሪ ሳልትን የጉዞ ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ታዋቂው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ያስቀመጡትን ጠንካራ የመከራከሪ ሀሳብ ስንመለከት እንዲህ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፣ “የትግራይ አካባቢ ህዝብ ዶባዎችን የራሱ አካል ማለትም ቀይ (ሴሚቲክ) አድርጎ ይመለከታቸው ስላልነበር ጥቁር ወይም ጸሊም (ኩሽቲክ) እያለ ያገላቸው ነበር” በማለት በጥናትና ምርምር ላይ የተደገፈ ግልጽ ምስክርነታቸውን መስጠታቸውን ጸሀፊውም የጠቀሱት እውነት ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ዶባዎች የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የህብረተሰብ ክፍል አካል እንዳልነበሩ ብቻ ሳይሆን በመሰረቱ ትግሬዎችም የነበሩ ህዝቦች አለመሆናቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያኑም ቢሆን እነዚህ ህዝቦች የኩሽቲክ ቋንቋ ቤተሰቦች መሆናቸው ላይ ምንም አይነት ጥርጣሬ የሚያጭር ነገር በአንድም የታሪክ፣ የስነ-ልሳንም ሆነ የስነ-ሰብ ተመራማሪ አልተጠቀሰም ብቻ ሳይሆን የአሁኑ ጸሀፊም ዶባዎችን ወደ አፋር ብሔረሰብ ለማስጠጋት ሞከሩ እንጂ በእርግጠኝነት ትግሬዎች ናቸው ሊሉ አልደፈረም፡፡

ሆኖም የዶባዎች የቅርብ ጎረቤት የሆነው የትግራይ ብሔር ህዝብ ደግሞ በዋነኛነት የሴሜቲክ ቋንቋ ቤተሰብ መሆኑ በቋንቋና ስነ-ልሳን ምሁራንም ተረጋግጦ ያደረ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ህዝቦች (ዶባዎች) የአፋር ብሔረሰብ አካልም ያልነበሩ መሆናቸውም ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ በታች በተቀመጠው ምሳሌ ለማየት እንደምንሞክረውም ዶባዎች (ቀደምት ያራያ ህዝቦች) በዘራያቆብ ልጅ በበዕደማሪያም ከፍተኛ የሆነ ዘመቻ ተከፍቶባቸው በነበረበት ወቅት ሳይቀር የአፋር ሱልጣን ለበዕደማሪያም አግዞ ዶባዎችን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ጥረት አደረገ እንጂ ከዶባዎች ጎን በመሰለፍ ወገኖቹ የሆኑትን ዶባዎች ከጥፋት ለመታደግ በተቃራኒው ቆሞ ሲዋጋም ሆነ ለእነዚህ ህዝቦች ጊዜያዊ ከለላ ወይም መጠለያ እንኳ ሲሰጣቸው አልተስተዋለም፡፡

ስለሆነም ዶባዎች የአፋር ብሔረሰብ ህዝብ አካል ቢሆኑ ኑሮ የአፋር አስተዳዳሪዎች (ሱልጣኔቶች) የራሣቸው ብሔረሰብ አካል የሆኑትን ዶባዎች በመውጋት ሀብትና ንብረታቸውን ለመዝረፍና ወገኖቻቸውንም መጠለያ ለማሳጣት ያን ያህል ተግተው አይንቀሳቀሱም ነበር ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የበዕደማርያም ጦር ቀደም ሲል በዶባዎች የተጠናከረ ጥቃት ሳቢያ በደረሰበት ተደጋጋሚ ሽንፈት ምክንያት በእልህና በቁጭት ተነሳስቶ ይበልጥ ተደራጅቶና ተጠናክሮ በመምጣት ጭምር በዶባዎችና በአካባቢው ቀደምት ህዝቦች ላይ በከፈተው የተጠናከረ ጦርነት ዶባዎችንና የአካባቢውን ቀደምት ህዝቦች ማሸነፍ ቻለ፡፡

ይህንን አጋጣሚ በመጠቀምም ንጉስ በዕደማሪያም በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዘመቻ ወቅት በሰራዊታቸው ላይ የደረሰውን ሽንፈት ተበቀሉ፡፡ ያለምንም ርሕራሔና በጭካኔ መንፈስ ተነሳስተውም በዶባዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊና አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ቂም በቀላቸውን ተወጡ፡፡ በዚህ ወቅት ነበር ከበዕደማሪያም ጦር የበቀል ቅጣት ለመዳን የፈለገ አንዳንድ የዶባ ማህበረሰብ አባላት ወደ አፋር አካባቢ በመሄድ ከበቀል እርምጃው ለማምለጥ ሲሞክሩ የአፋር ሱልጣኔቶች ተቀብለው መጠለያ ከመስጠትና ከንጉሱ የበቀል እርምጃ እንዲድኑ ከመርዳት ይልቅ ንጉስ በዕደማሪያምን ለማስደሰትና ለንጉሱም ያላቸውን ታማኝነት በተግባር ለማረጋገጥ ሲሉ ዶባዎችን አሳደው ይገድሏቸው እንደነበር የታሪክ ፀሀፊዎች በግልጽ አስፍረው የምናገኘው፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ በቀጣዩ ስራችን ላይ በዝርዝር የምንመለከተው ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዶባዎች ማንነት ወራሽ የሆኑት ራያዎችና የቅርብ ጎረቤቶቻቸው አፋሮች አንዱ በሌላኛው ላይ በመዝመት ንበረት ለመዝረፍም ሆነ የሰው ህይወት በማጥፋት ጭምር የጀግንነት ውርሳቸውን ለማረጋገጥ ያደርጉት የነበረውን ጥረት ስንመለከት እነዚህ ህዝቦች በፍጹም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸውን አሳውቀው ያደሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ረገድ የትዝታዋ ንግስት በዛወር አስፋው ቀደም ሲል በአንቀረቀረችው የትዝታ ዜማዋ ላይ የተጠቀመችው የግጥም ስንኝ ለዚህ ንዑስ ምዕራፍ መቋጫነት በእጅጉ ሊያገለግል ይችላል ብዬ ስላመንሁ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡

የማነሽ ይሉኛል የማን ልበላቸው?

ብቻየን ብቆይስ ምን አስጨነቃቸው፡፡

ልብ የፈቀደውን እስኪለግስ ቀኑ፣

መኖርም ይቻላል የማንም ሳይሆኑ፡፡

መጾም መታገሱን ከቻለልኝ ሆዴ፣

ይከረም የለም ወይ ሁለት ወር ኩዳዴ፡፡

የማነሽ ይሉኛል የማን ልበላቸው?

ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ሆዴን አቆሰለው፡፡

አይቻልም ወይ መኖር የማንም ሳይሆኑ፣

ልብ የፈቀደውን እስኪለግስ ቀኑ፡፡

የማንም አይደለሁ የማነሽ ይሉኛል፣

ከተረት ከወሬ እስኪ ምን ይገኛል፣

ከዳንኝነት ሚዛን ሙግት አደባባይ፣

ለፍቅር አይኮን እንደ ሽፍጥ እንደ አባይ፡፡

የሰው ሁሉ ምርጫው እንደሰው ይለያል፣

*የአንዱ ቆንጆ ላንዱ አይሆነው ይሆናል፡፡*

*የማንም አይደለሁ ለጊዜው የእኔው ነኝ፣*

*ጊዜ እስከሚቸረኝ ሆኘው የሚሆነኝ፡፡*

*ዝምታ ሽብቦ ሲጠፋ ደስታ፣*

*የእገሌ ናት መባል ይሆን ወይ ግዴታ፡፡*

*ስለሆነም ዶባዎች ከመነሻውም ዶባዎች እንጂ የአፋር፣ የኦሮሞ አሊያም የትግራይ ብሔር አካል ሊሆኑ እንደማይችሉ ከላይ በማስረጃ ተደግፎ ከቀረበው አጭር ማብራሪያ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት ግን ራያዎች እኛ ከመነሻው ዶባዎች እንጂ ትግራዮች፣ አፋሮች አሊያም ኦሮሞዎች አይደለንም ሲሉ ከላይ እንደተገለጸው በተጨባጭ ስላልሆኑ ነው እንጂ ከእነዚህ ብሔሮች ውስጥ አንዱን ሆኖ መገኘት ስለማይፈልጉት ብሎም ስለሚጠሉት እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዛም አልፎ አሁን ላይ ራያዎች የአንድ ብሔር አካል ብቻ ሳይሆኑ የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የአማራና የአገው ህዝቦች ውህደት በትክክል የሚንጸባረቅባቸው እውነተኛ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን ማንም አሌ ሊለው የሚችለው ጉዳይ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ቀጣዩ የምርምር ስራ ማተኮር የሚኖርበት ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ታዲያ ዶባዎች ይናገሩት የነበረው ቋንቋ ምን ይመስል ነበር በሚለው መሰረተ ሀሳብ ላይ አተኩሮ በቀደመው ዘመን ዶባዎች ይግባቡበት የነበረውን ቋንቋ ማንነት መለየት ይሆናል፡፡*

**እንደመውጫ**

*አቶ ተሾመ በመጀመሪው ክፍል መግቢያ ላይ አጽንኦት ሰጥተው ለመግለጽ እንደሞከሩት አንድ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተዳፍኖ በኖረው በዶባዎች (ራያዎች) እውነተኛ ታሪክ ዙሪያ ሁለት መጸሀፍት ታትመው ለአንባቢያን መድረሳቸው በጣም ያስገረማቸው ይመስላል፡፡ የትኩረታቸው ማዕከል ስላልሆነ ይሆናል እንጂ እሳቸው ይህን ጽሁፍ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ማውጣት ከመጀመራቸው በፊት በነበሩት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ቀደም ሲል ታትመው የወጡትንና በራያ ህዝብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹ ኢትዮጵያዊያንም ጭምር ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያገኙትን ነገር ግን በወግ አጥባቂ የትግራይ ሰዎች ዘንድ በመጥፎነት የተፈረጁትን መጻህፍትና በተመራቂ ተማሪዎች የተሰሩ ምርጥ ጥናታዊ ጽሁፎችን ሳይቀር ማሳጣትን አላማው ያደረገ የመልስ ምት የሚመስል ሌላ ሶስተኛ መጽሀፍ ጉማ በሚል ርዕስ ራያ ቆቦን ወደ ጎን በመተው ላይ የተመሰረተ የራያ ህዝብ ታሪክ በትግርኛ ቋንቋ ተጽፎ በአላማጣ ከተማ አስተዳደር የገንዘብ ድጋፍ መታተሙንና ለንባብም መብቃቱን አልሰሙ ይሆናል ብሎ መናገር ይከብዳል፡፡*

*ይኽ መሆኑ በእጅጉ ያስገረማቸው ነገር ደግሞ እነዚህ በአማርኛ ቋንቋ ተጽፈው የታተሙትና በአሁኑ ወቅት ገበያ ላይ የሚገኙት መጽሀፍት የራያ ህዝብ ማንነትና ፖለቲካዊ ተጋድሎ ላይ ያተኮሩ፣ ባህልና ወጉን በጥልቀት የዳሰሱና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄውን ከፍ አድርገው ያነሱ ከመሆናቸውም በላይ በቀደምት የራያ ህዝቦች ላይ ግፍ የፈጸሙ ገዥዎችን ሴራ በማጋለጥ እርቃናቸውን እንዲቀሩ በማድረጋቸው እንዲሁም የአሁኑን የራያ ህዝብ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚያነቁ ሆነው በማግኘታቸው ስጋት ገብቷቸው እንጂ የታሪክ ተመራማሪዎችም ሆኑ በራያ ህዝብ ታሪክ ዙሪያ መጽሀፍ ያሳተሙና ጥናታዊ ጽሁፍ ያዘጋጁ ግለሰቦች ስለዶባዎች ማንነት የተለያዩ*

መላምቶችን ማስቀመጣቸው ያን ያህል አሳስቧቸው እንዳልሆነ ከማጠቃለያ ሀሳባቸው ላይ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም አቶ ተሾመ መነሻቸውን የዶባዎች ታሪክ ላይ ለማስመሰል ሞክሩ እንጂ ማሳረጊያቸውን እነዚህ የራያ ቀደምት ህዝቦች የአፋር ብሔረሰብ አካል እንደሆኑ በማድረግ አሁን ግን እነዚህ ህዝቦች አብዛኛዎቹ ትግርኛ ተናጋሪዎች በመሆናቸው ወደ ትግራይ ክልል መካተታቸው ተገቢም ፍትሀዊም ነው ለማለት ይዳዳቸዋል፡፡ የሚገርመው ነገር የዶባዎችን ታሪክና ማንነት በማብራራት ሽፋን የአሁኑን የራያ ህዝብ ወቅታዊ ሁኔታ ከመልካም አስተዳደር ችግር ጋር በማዛመድ ብቻ ለማድበስበስ ለምን ያን ያህል ደከሙ የሚለው ሀሳብ ለጊዜው ባይገባንም ስለህዝቡ ወቅታዊ ብሶት፣ መሰረታዊ መብት መታፈንና ስለእውነተኛ ማንነቱ ዕውቅና ማግኘት ምንም ነገር ሳይሉ የተወሰኑ የግለሰብ ስሜቶችን ብቻ አንስተው ጥያቄውን ከመልካም አስተዳደር ችግር ጋር ብቻ ለማያያዝ መሞከራቸው የሚያስገነዝበው ድሮም ቢሆን የጽሁፋቸው አላማ ሌላ መሆኑን ነው፡፡ ሌላውና በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ሊያሰኝ የሚችለው ሀሳብ ትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙት ኩናማዎች በቁጥር ከ2000 የማይበልጡ ቢሆኑም በክልሉ መንግስት ዕውቅና አግኝተው ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩና ቋንቋቸውም እንዳይጠፋ ጥረት በሚደረግበት ሁኔታ ከ10,000 የማያንስ ቁጥር ያላቸው የራያ ኦሮሞዎች፣ ከ10,000 በላይ የሚሆኑ አገዎችና ከ70,000 በላይ ቁጥር እንዳላቸው የሚነገርላቸው አማሮች በቋንቋቸው እንዳይማሩ፣ እንዳይዳኙና ራሳቸውንም በራሳቸው እንዳያስተዳድሩ መከልከላቸው ሊያሳስባቸው ሲገባ እና ምን ይጠበስ በማለት ለትግራይ ክልል የሚጠቅም ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የመብት ረገጣው አስፈላጊ ነው የሚል አንድምታ ያለው አቋም ያራምዳሉ፡፡

ጸሀፊውም ሆኑ መሰሎቻቸው ያልገባቸው ነገር ቢኖር ግን የራያ ህዝብ ታሪኩን ጠንቅቆ የሚያውቅና ለማንነቱ ቀጣይነትም አበክሮ የሚንቀሳቀስ እንጂ ማንም ሰው ከሜዳ ተነስቶ እንዲህ ነህ ስላለው በቀላሉ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆኑን ነው፡፡ በነሱ ቤት የራያ ህዝብ ከትግራይ ብሔር ህዝብ ታሪክ ተለይቶ መታየት የለበትም፣ እንዲያውም የራያ ህዝብ የተጋድሎ ታሪክ ጎልቶና ራሱን ችሎ ሲወጣ አይናቸው ደም የሚለብስ መሆኑን ቀደም ሲል የተጠቀሱት ማለትም "የራያ ህዝብ ባህልና ታሪክ"ም ሆነ "የራያ ህዝብ የማንነት ጥያቄና የማዕከላዊ መንግስታት ምላሽ ከአጼ ዮሀንስ 4ኛ እስከ ኢህአዴግ" የሚሉት መጽሀፍት ታትመው እንደወጡ ገበያ ላይ በነጻነት ስሜት እንዳይሸጡና ለአንባቢያንም በወቅቱ እንዳይደርሱ ለማድረግ የተደረገው የተቀናጀ እንቅስቃሴ አመላካች ነው፡፡